ቀን፡ 14/03/2009 ዓ.ም

# የትግራይ ተወላጆች ናቸው በሚል የእርሻ ኢንቨስትመንታችን ኢላማ ገብቶ በቢሮክራሲው እንዲዳከም እየተደረገ ነው!

የጋምቤላ ህዝብ ወኪል የሆነው የጋምቤላ ህዝቦች ብሄራዊ ክልላዊ መንግስትና የፌደራል መንግስት ክልሉን በማልማት የክልሉ ህዝብ የንሮ ደረጃ ለማሻሻል ቆራጦች የሆኑና ራሳቸውም ተጠቃሚ የሚያደርጉ ልማታዊ ዜጎችና አጋሮች በክልሉ ልማት እንዲሳተፉ በይፋ ጋበዙ።

ጋምቤላ ታዳጊ ክልሎች ተብለው ከሚጠሩ የሃገራችን ክልሎች በጣም በዝቅተኛ ደረጃ የምትገኝ ክልል ናት። የተሻለ ምቾት፣ ብዙ ባለሃብት ከሰፈረባትና ብዙ ገንዘብ ከሚንሸራሸርባት ከመዲናችን አዲስ አበባ ጠረፍ አከባቢ ያለችው ጋምቤላ ከ780 ኪሎ ሜትር በላይ ርቃ ትገኛለች። የክልልና ፌዴራል መንግስት ጋምቤላ ሰፊ ለም የመሬት ሃብት እንዳላት በማውሳት ከመሬትዋ ፍሬ አፍርተው ለገበያ በማቅረብ የሚያለምዋትና የምታለማቸው ዜጎች ለማግኘት በሰፊውና በተደጋጋሚ ጥሪ አቅርቧል።

አቤት! የኛ ሃገር ምድር! የመንግስታችን ፖሊሲና የልማት አቅጣጫ ሰንቀን በላብ በወዛችን ጥረን ግረን አብረንሽ እናድጋለን ብለን የሞቀ ጎጃችንና ቤተሰቦቻችን ተሰነባብተን ጥሪውን የተቀበልን ጥቂት ዜጎች የእርሻ ኢንቨስተሮች ለመሆን የዛሬ ስምንት ዓመት ገደማ ጋምቤላ ደረስን።

እርሻ ከባድ የኢንቨስትመንት ዘርፍ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ከተማ የለመደ ባለሃብት የማይመርጠው ዘርፍ መሆኑ ይታወቃል። ቢሆንም ከጋምቤላ ህዝብና መንግስት ጋር ተባብረን ለፍሬ እንበቃለን ብለን ተስፋ የሰነቅን ልማታዊ ዜጎች ከየአቅጣጫው መጥተን ጋምቤላ ተገናኘን። ጋምቤላም ቀድሞ ለደረሰ ቅድሚያ በሚል መርህ እንኳን ደህና መጣቹህ ብላ ታስተናግደን ጀመር።

የጋምቤላ መሬቶች ለሜካናይዝድ እርሻ ልማት የተዘጋጁ አይደሉም። እኛ ወደ እርሻ ኢንቨስትመንት ስንገባ በከተማዋ ከሁለት ያልበለጡ ሆቴሎች፣ ከከተማዋ ወደ እርሻ ቦታ የሚወስድ መንገድ አልነበረም። ከሁሉም በላይ አስተማማኝ ያልሆነ ፀጥታ፣ የጉልበት ሰራተኛ ያለመኖር፣ ንፁህ ዉሃ ያለማግኘት፣ መብራትና ሌሎች መሰረተ ልማቶች ባልነበሩበት ሁኔታ ነው። ታድያ ቀድም ባለ የህይወት ጉዟችን በሌላ ቦታ ያፈራነው ሃብትና ንብረት አፍስሰን ክልሉን ለማልማት የደፈርን ቆራጥ ኢትዮጵያውያን በሞፈርና በቀንበር ሳይሆን በትራክተር፣ በበሬ ጉልበት ሳይሆን በነዳጅ

ሃይል ሜካናይዝድ ፋርም ለመፍጠር በጋምቤላ መሬቶች ተግባራዊ እንቅስቃሴ ጀመርን። ይህ ያደረግንበት ጊዜ ስለጋምቤላ መልካም ምስል ባልነበረበት ጊዜ መሆኑ ማስታወስ ተገቢ ይመስለናል።

እንዲህ ባለው ሁኔታ ውስጥ ሆነን ተፈጥሮን ለእርሻ ምቹ ለማድረግ ከተፈጥሮ ጋር ልማታዊ ትግል አካሄድን። መሰረተ ልማት በሌለበት የመሬት ልማት ለማከናወን ህይወት፣ አካልና ንብረት ማጣት ለልማቱ የሚከፈል ዋጋ ነበር። የመሬት ልማት ስራውን ስትታገል ከርመህ አንድ የአገሪቱ ልማት የማይፈልግ ክፉ ወይም ነገሩ ያልገባው ሰውም ሊጎዳህ ይችላል። በመሆኑም ብዙ አይነት ሰው ሰራሽ የደህንነት ችግሮች ነበሩ። ይህም ታልፏል።

ለእርሻ ዝግጁ ያልሆኑ ሰፋፊ ለም መሬቶች የእርሻ ማሳ እንዲሆኑ ለማልማት የሚከናወን ተግባር እንዲሁ በጥላ ስር ሆነህ እቃን በመሸጥና በለወጥ እንደሚገኝ ሃብት ተመኝተህ የምትገባው አይደለም። አዲስ የአየር ፀባይ አዲስ መንደር ብዙ ያልተጠበቀ ነገር መጋፈጥ ግድ ይላል፤ ቆራጥነትም ይጠይቃል።

ከዚህ በላይ ዘር መሬት ላይ በትነህ፣ በስብሶ፣ ተመልሶ በቅሎ፣ አረም ታርሞ፣ ከነብሳት ታድገህ፣ ታጭዶ፣ ተወቅቶ፣ ለገበያ ቀርቦ ይሄ ሁሉ ረጅም መንገድ ተጉዞ ከቀናህ የበተንከውን ትሰበስባለህ፤ ለፍሬ ለአምሃ ትበቃለህ። ገበያና ኢንዱስትሪ ይንቀሳቀሳሉ። እርሻና የእርሻ ሰዎች ህይወት እንዲህ መሆኑ የገባን ዜጎች የሃገራችንን ፀጋ አነቃቅተን ወሳኝ የኢኮኖሚ አውታር የሆነውን የእርሻ ኢንቨስትመንት ተሰማራን ።

የጋምቤላ የልማት ጥሪ ተቀብለን በልበ ሙሉነት የሄድን ኢንቨስተሮች ሃብትና ንብረታችን ይዘን እንጂ የመንግስት ብድር አመቻችተን እንዳልነበረ መታወቅ አለበት። ይሄ እዉነታ መረሳት የሌለበት ሃቅ ነው። በተጨማሪ ኢንቨስተሩ ወደ ተሰጠው የእርሻ ቦታ ይሁን ወደ አከባቢው የሚወስድ የተሰናዳ መንገድ አይታሰብም። መደበኛ ሆነ ተንቀሳቃሽ ስልክ አልነበረም። በስራ ላይ ዉለው አቅጣጫ ስተው በመከላለከያ አብሪ ጥይት እየተፈለጉ የተገኙ ኢንቨስተሮች ብዙ ናቸው። ይሄም ለሃገር ልማት የተከፈለ ዋጋ ነው።

ብዙ የመሰረተ ልማትና የአቅርቦት እጥረት ባለበት አከባቢ በዘመናዊ የእርሻ መሳሪያና በሰው ሃይል ለማልማት ዘመናዊ እርሻ እውን ለማድረግ የታገልን ዜጎች የከፈልነው መስዋእትነት አሁን ጋምቤላ የሞቀች ከተማ እንድትሆን ብዙ መንደሮችም ሰላም እንዲሆኑ ረድቷታል ቢባል ደፍሮ ውሸት የሚል ፍጡር አይኖርም። እኛ የጋምቤላ የእርሻ ኢንቨስተሮች የክልሉ ኢንቨስትመንት ህያው ለማድረግ የከፈልነው ዋጋ በጣም ብዙ እንዲሁም ዘርፈ ብዙ መሆኑ መዘንጋት የለበትም ።

GAMBELLA AGRICULTURAL INVESTORS COOPERATIVE